
www.purposeblacketh.com





# PURPOSEBLACK ETHIOPIA

## የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

ለሦስተኛው የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርብ ዓመታዊ ሪፖርት



# የፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ትሬዲንግ አ.ማ
# የባለአክሲዮኖች 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

የካቲት 7 ቀን 2016 ዓ.ም
ከኢንቨስትመንት ወደ ትርፍ
የ25 በመቶ ትርፍ ክፍፍል ፍኖተ ካርታ

PurposeBlack ETH Trading S.C.
3rd Shareholders General Assembly
February 15, 2024 G.C

## The Turn-Around General Assembly
## The Road Map to 25% ROI

# ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

## ለሦስተኛው የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርብ ዓመታዊ ሪፖርት

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ኑ አብረን እንሥራ ፤ አብረን በመሥራት የኑሮ ውድነትን በኢትዮጵያ ታሪክ እናደርገለን ፤ ብሎም ለመላው ጥቁር ሕዝብ ተምሳሌት የሚሆን ታሪክ እንሠራለን በሚል ጽኑ መርሕ የሚንቀሳቀስ በሕዝብ ባለቤትነት የተመሠረተ ግዙፍ አገሪዊ የቢዝነስ ተቋም ነው። ከዓላማውም ግዙፍነት የተነሣ ይህንኑ ዓላማዬን ያስፈጽሙልኛል ብሎ ባመነባቸው ግዙፍ ኢንቨስትመንቶች ላይ በመሳተፍ በትግበራ ላይ ይገኛል።

ኢንቨስትመንቶቹ በአብዛኛው ትኩረታቸውን ያደረጉት በግብርና የእሴት ሰንሰለት ላይ በተመሠረቱ የልማት ተግባራት ላይ ነው። እነዚህም ትላልቅ የግብርና ልማት ኢንቨስትመንት ሥራዎች፣ የግብርና ምርቶች ማቀነባበር ሥራዎች፣ እና የግብርና እና ተያያዥ የዕለት ፍጆታ ምርቶች ስርጭትና ግብይት ሥራዎች ናቸው።

እነዚህን በግብርና የእሴት ሰንሰለት ላይ ያተኮሩ ሥራዎች በተቀናጀ መልኩ መሥራት ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ምርት ከአምራቹ በቀጥታ ለሸማቹ የሚደርስበትን ሥርዓት በመዘርጋት  በአንድ በኩል አምራቹ ገበሬ የላቡን ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ ገቢውን እንዲጨምርና ሕይወቱን እንዲያሻሽል ለማስቻል፤ በሌላ በኩል የተረጋጋ የግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር በማድረግ የሸማቹን ኅብረተሰብ የኑሮ ጫና መቀነስ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። በሒደትም የታሰበውን የኑሮ ውድነት በኢትዮጵያ ታሪክ ለማድረግ መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር ይሆናል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ እነዚህን በይዘታቸው ወጥ የሆኑና በተቀናጀ መልኩ ሲተገበሩ በኢትዮጵያ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸውን ሥራዎች በከፍተኛ ርብርብ በመሥራት ላይ ይገኛል። ተቋማችንም በሒደት ያከናወናቸውን ተግባራት አፈጻጸም ለመገምገም ያስችለው ዘንድ የሚከተሉትን ሰምንት የአምስት ዓመት ግቦች አጽድቆ ሥራዎቹን እያከናወነ ይገኛል።

ግቦቹም፦

- በኢትዮጵያ ትልቁ ኮሜርሻል የእርሻ ክላስተር መሆን
- በኢትዮጵያ ትልቁ የሸማቾች ብድር አቅራቢ መሆን
- 50 የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎችን መገንባት
- በኢትዮጵያ ትልቁ የፍጆታ እቃዎች አከፋፋይ መሆን
- 1000 የከገበሬው ሱፐርማርኬቶችን መገንባት
- 5000 ሄክታር መሬት በእርሻ ማልማት
- በኢትዮጵያ ትልቁን የበይነ መረብ(ኢኮሜርስ) ገበያ መገንባት
- በዓለም ትልቁን የጥቁር ሕዝብ ሚዲያ መገንባት
- በኢትዮጵያ ትልቁ ቤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ አቅራቢ የሪል እስቴት ኩባንያ መሆን ሲሆን

በዚህ ሪፖርት አማካይነትም እነዚህን ለማስፈጸም ይበጃናል ያላቸውን ግቦች፣ ስልቶችና በእነዚህ የአተገባበር ስልቶች አማካይነት የተመዘገቡ ውጤቶችን በዝርዝር የምናቀርብ ይሆናል።

## የግብርና ልማት ሥራዎች

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በግብርና ልማት ኢንቨስትመንት ሥራዎቹ የሚከተላቸው ስልቶች ሦስት ዓይነት ሲሆን እነዚህም፦

- አንደኛው ገበሬዎችን በክላስተር በማደራጀት እና የተቀናጀ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን ከትርፍ ነጻ በሆነ መልኩ በመስጠት የኩታገጠም እርሻዎችን ማሳረስ ፤ በሒደቱም ምርቶቻቸውን በመቀበል በቀጥታ ለሸማቹ ማቅረብ።

- ሁለተኛው በሰፋፊ የግብርና ልማት ኢንቨስትመንት ላይ ከተሳተፉ ባለሃብቶች ጋር በጋራ ማልማትና እኩል የትርፍ ተካፋይ መሆን።

- እንዲሁም ሦስተኛው ከክልል መንግሥታት ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት መሬቶችን በሊዝ በመውሰድ በራስ አቅም ማልማት ናቸው።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በእነዚህ ሦስት የማስፈጸሚያ ስልቶች አማካይነት በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ አመርቂ የሚባሉ ሥራዎችን በመሥራት ላይ የሚገኝ ሲሆን የሚከተሉትም ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

- ገበሬዎችን በክላስተር በማደራጀት እና እጅግ ተፈላጊ የሆነ የተቀናጀ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ከትርፍ ነጻ በሆነ መልኩ በማቅረብ የኩታገጠም እርሻዎችን ማሳረስ በሚለው ስልቱ እስከአሁን 55 የሚሆኑ የግብርና ክላስተሮችን ማደራጀት የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አምስቱን ወደ ሥራ በማስገባት ምርት መሰብሰብ ተችሏል። በዚህ ስልት አማካይነት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት አንድ ሚሊዮን ገበሬዎችን የሚያቅፉ 10,000 የገበሬ ክላስተሮችን ማደራጀት እና ከ500,000 ሄክታር በላይ የሚሆን መሬትን በኩታገጠም በማረስ ወደ ኮሜርሻል እርሻነት በመቀየር ዓመቱን ሙሉ ማሳረስ እና ምርት መሰብሰብን አንኳር ዕቅዱ አድርጎ ይዟል።

- በሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት ከተሰማሩ ባለሃብቶች ጋር በጋራ ማልማት በሚለው ስልቱ እስከአሁን አራት ከሚሆኑ ኩባንያዎች ጋር በውል በተሰረ ስምምነት አማካይነት የእርሻ ሥራዎችን በጋራ እየሠራን ሲሆን እነዚህም በደቡብ ኦሞ ኛንጋቶም ወረዳ 1,000 ሄክታር የአስቴር እርሻ እና 300 ሄክታር የደንሞቴ እርሻ፣ በአርባምንጭ ዞን ምዕራብ አባያ ወረዳ 30 ሄክታር የተቀናጀ የእንስሳት እርባታና የመኖ ልማት የሚካሄድበት የደንሞቴ እርሻ፣ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ አርሲ ዞን በቆጂ ወረዳ 372 ሄክታር የሚለማበት የበቆጂ እርሻ ልማት ፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በሆለታ ወረዳ የባዝሚን የደሮ እርባታ ፕሮጀክትን ከባለሃብቶች ጋር በጋራ እያለማን እንገኛለን። በእነዚህ የጋራ እርሻዎች አማካይነት የሚካሄደው የግብርና ልማት ፕሮጀክት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ሲሆን የትልልቆቹ እርሻዎች የመስኖ ጥናት ሥራ ተጠናቆ የመስኖ መሰመር ዝርጋታ ሥራ በተቀላጠፈ መልኩ በመከናወን ላይ ይገኛል። በተያያዘም የሠራተኞች መኖሪያ ካምፖች ግንባታ እና ሌሎች ተያያዥ የእርሻ መሠረተ ልማቶች ግንባታ ሥራዎች በመካሄድ ላይ ናቸው።

• ከክልል መንግሥታት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን በሊዝ በመውሰድ ማልማት በሚለው ስልቱ አማካይነት ለተለያዩ የክልል መንግሥታት የመሬት ጥያቄ በጽሑፍ በተዘጋጀ ፕሮፖዛል አማካይነት የቀረበ ሲሆን አብዛኛዎቹ ጥያቄ የቀረበላቸው ክልሎች የኩባንያውን ግዘፍ አገራዊ ዓላማ በመረዳት የኢንቨስትመንት መሬት ለማቅረብ በጎ ምላሻቸውን ሰጥተውናል። ጉዳዩም በሒደት በጥናት እና በመሬት መረጣ ላይ እንደሚገኝ አረጋግጠውልናል። ከዚህ አንጻር መልካም ምላሻቸውን የሰጡን የሲዳማ ክልል ፣ የሱማሌ ክልል ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሰሜን ኦሞ ዞን እና የወላይታ ዞን ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ፣ የቦንጋ ዞን ፣ በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሃድያ ዞን ይገኙበታል። የአፋር ክልል 1,000 ሄክታር መሬት በሊዝ በመስጠት ቀዳሚውን ስፍራ የያዘ ሲሆን በተሰጠን መሬት ላይ ከፍተኛ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንገኛለን።

• ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የክልል የልማት ማኅበራት ፓርትነርሺፕ ፕሮግራም /DAPP– Development Associations Partnership Program/ በሚል ሰፊ እንቅስቃሴ የጀመረ ሲሆን በዚህ ፕሮግራም አማካይነት ከሁሉም የክልል መንግሥታት የልማት ማኅበራት ጋር በመሆን ሰፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንቶች ላይ ለመሳተፍ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ ፕሮግራም በቅርቡ የተጀመረ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከስምንት የክልል የልማት ማኅበራት ጋር የጋራ ሥራ ለመሥራት ስምምነት ላይ ተደርሶ የመግባቢያ ሰነዶችን በመፈራረም ላይ እንገኛለን።

እነዚህም፦

- የአማራ ልማት ማኅበር /ORDA–Organization for Relief & Development of Amhara/
- የኦሮሚያ ልማት ማኅበር /ODA: Oromia Development Association/
- የትግራይ ልማት ማኅበር /REST: Relief Society of Tigray/
- የሲዳማ ልማት ማኅበር /SDA: Sidama Development Association/
- የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ልማት ማኅበር /SEPDA: Southern Ethiopian People Development Association/

- የሶማሌ ልማት ማኅበር /SDA: Somali Development Association/
- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ልማት ማኅበር /BEGDA: Benishangul Gumuz Development Association/ እና
- የአፋር ልማት ማኅበር /ADA: Afar Development Association/ ናቸው። በዚህ ፕሮግራም አማካይነት ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በመላ አገሪቱ የተሳለጠ የገበሬ ክላስተር የኩታገጠም እርሻ ሥራ ለመሥራት ያቀደ ሲሆን ፤በሒደቱም በሚሊዮን ሄክታር የሚቆጠሩ ከዚህ በፊት ያልለሙ ወይም በአግባቡ ያልለሙ መሬቶችን ወደ ኮሜርሻል እርሻነት በማስገባት ዓመቱን ሙሉ የሚታረሱበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ትልቅ ዓላማ ሰንቆ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

- በዚህ በግብርና ልማት ኢንቨስትመንት ዘርፍ የታቀዱ ተግባራትን እጅግ በተሳለጠ መልኩ ለማካሄድ እንዲያመች የውስጥ የማስፈጸም አቅማችንን ለማሳደግ በከፍተኛ ርብርብ ላይ የምንገኝ ሲሆን፣ ከዚህ አንጻር የአግሪ ኢኖቬሽን ክፍል ፣የመስኖ ጥናትና ዝርጋታ ክፍል፣ የአፈር ምርመራ ክፍል ፣ የግብርና ሜካናይዜሽን እና ምሕንድስና ክፍል መቋቋም ተጠቃሾች ናቸው። በተያያዘም 9 ትራክተሮችና 5 ሎደሮች በግዢ ወደ ሥራ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ይህ የውስጥ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ተግባር እጅግ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

- በዚህ በግብርና ልማት ኢንቨስትመንት የሥራ ዘርፍ ውስጥ ቁጥራቸው ከ1500 በላይ የሆኑ አብዛኛዎቹ ለረጅም ዓመታት መሬት የወረደና በተግባር የተፈተነ ልምድ ያላቸው የግብርና ባለሙያዎች ተመድበው እየሠሩ ሲሆን ይህ ቁጥር በሒደት በከፍተኛ ደረጃ የሚጨምር ይሆናል።

## የግብርና ምርቶች ማቀነባበር ዘርፍ

ይህ ዘርፍ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንጻር ቁልፍ ሚና የሚጫወት ዘርፍ ሲሆን የግብርና የእሴት ሰንሰለቱን ሥራ ከማሳለጥ አንጻር ሚናው ከፍተኛ ነው። እንደሚታወቀው አብዛኛዎቹ የግብርና ምርቶች በተለይም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በተፈጥሮ በቀላሉ ለብልሽት ተጋላጭ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ገበሬው የምርቱን ዋጋ ከመወሰን አንጻር ያለው አቅም እጅግ የተመናመነ እንዲሆን በማድረግ በስግብግብ ነጋዴዎችና እሴት በማይጨምሩ ደላሎች እጅ እንዲወድቅ አድርጎታል።

ከዚህም በተጨማሪ በአገሪቱ ምርትን ከመሰብሰብ፣ ከመከዘን እና ለገበያ ከማቅረብ ጋር የተያያዙ የግብርና መሠረተ ልማቶች ያሉበት የእድገት ደረጃ እጅግ ኋላቀር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከድህረ-ሰብሰባ ጋር የተያያዘ የምርት ብክነት /Post Harvest Loss/ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ጥናቶች አረጋግጠዋል። ይህ አሃዝ በአብዛኛዎቹ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ እስከ 40 ከመቶ የሚደርስ ሲሆን እንደ ቲማቲም ባሉ ምርቶች ላይ ደግሞ ከ50 በመቶ በላይ መሆኑን መረጃዎች ያረጋግጣሉ። በመሆኑም ይህንን አምራቹ ገበሬ ላይ የተጋረጠ አንገብጋቢ ችግር በመፍታት ምርትና ምርታማነቱን እንዲጨምር ከሚያደርጉት ቁልፍ ተግባራት አንዱ የግብርና ምርቶች ማቀነባበር ሥራ ነው።

ይህ የግብርና ምርቶች ማቀነባበር ሥራ በምርቶች ላይ እሴት መጨመር እና የመደርደሪያ ላይ ቆይታ ጊዜያቸውን ለማራዘም እጅግ ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን ፤ የምርት ብክነትን ከመቀነስ አንጻርም ሆነ የሰግብግብ ነጋዴዎችን እና የደላላውን የምርት ዋጋ የመወሰን ተጽዕኖ ለቅም ከማደከም አንጻር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። በሒደትም ለአምራቹ ገበሬ እፎይታን የሚሰጥ ተግባር ይሆናል። በመሆኑም የኩባንያችን ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አንዱ ቁልፍ የሥራ ዘርፍ እንዲሆን ተደርጓል።

ይህንን የሥራ ዘርፍ በተገቢው መልኩ ለመተግበር ፐርፐዝብላክ ሁለት ስልቶችን የነደፈ ሲሆን እነኚህም፦

- አንደኛ 10,000 የሚሆኑ አነስተኛ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ክላስተሮችን /Micro-processing schemes or Agro-processing clusters/ ማደራጀት እና በማኅበር ሆነው የተለያዩ የግብርና ምርቶችን የሚያቀነባብሩበትን ሥራ በፋይናንስ እና በቴክኒክ መደገፍ ፤
- ሁለተኛ 50 የሚሆኑ ግዙፍ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን በማቋቋም ምርቶች ሳይበላሹ፡ እሴት ተጨምሮላቸው ለረዘመ ጊዜ በገበያ ላይ የሚቆዩበትን ሁኔታ ማመቻቸት የሚሉ ናቸው።

እነዚህ አንኳር ግቦች በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት እንዲፈጸሙ ዕቅድ የተያዘላቸው ሲሆን በሁለቱ የማስፈጸሚያ ስልቶች አማካይነት ፐርፐዝብላክ እስከአሁን ያስመዘገባቸው ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው።

- በአርባምንጭ ከተማ አንድ መለስተኛ የባልትና ምግቦች ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ተቋቁሞ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆን ስድስት ትላልቅ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን ለመገንባት የሚያስችል 25,000 ካሬ ሜትር ወይም 2.5 ሄክታር መሬት ከከተማዋ መስተዳድር በሊዝ ተረክበን ፋብሪካዎቹን ለመገንባት የቦታውን አጥር የማጠር ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

- በአዲስ አበባ ሁለት መለስተኛ የዳቦ መጋገሪያ ፕሮጀክቶች እና አንድ መለስተኛ የእንጀራ መጋገሪያ ፕሮጀክት ጀምረናል።

- በከተሞችና በገጠር መኖሪያ ቤቶች አካባቢ በሚኖሩ ነዋሪዎች እና በገጠር በክላስተር የተደራጁ የገበሬ ቤተሰቦች አማካይነት መለስተኛ የግብርና ምርቶች ማቀነባበር ሥራ የሚሠሩ በወጣቶችና ሴቶች የተደራጁ ማኅበራትን ለማቋቋም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እና የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመሥራት ላይ እንገኛለን።

- በተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለመሳተፍ በኦሮሚያ ክልል የቡልቡላ የተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና በሲዳማ ክልል የይርጋለም የተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርክን ቀርበን በማነጋገር አብሮ የመሥራት ዕቅዳችንን ያቀረብን ሲሆን በይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ሼዶችን ተረክበን ለማልማት የስምምነት ሒደቱ እየተገባደደ ይገኛል።

- ይህ የግብርና ምርቶች ማቀነባበር የልማት ዘርፍ ከፍተኛ የማኔጅመንቱን ትኩረት አግኝቶ የሚተገበር ዘርፍ ሲሆን አሁን ባለው ሒደት 10 የሚሆኑ ብቁ ባለሙያዎች ተመድበውለት እየሠሩ ይገኛሉ። ይህ የባለሙያ ቁጥር በቅርቡ በከፍተኛ ቁጥር የሚያድግ ይሆናል።

## የግብርና እና ተዛማጅ የዕለት ፍጆታ ምርቶች ስርጭትና ግብይት ዘርፍ

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ስግብግብ ነጋዴዎች እና እሴት የማይጨምሩ ደላሎች በምርት ዋጋ ተመን ማውጣት ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ በመቀነስ ሸማቹ ማኅበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ የዕለት ፍጆታ ምርቶችን እንዲያገኝ ለማድረግ ከነደፈው ቁልፍ የሥራ ዘርፍ ውስጥ አንዱ የዕለት ፍጆታ ምርቶች ስርጭት እና ግብይት ዘርፍ ነው። በዚህ የምርት ስርጭት እና ግብይት ዘርፍ ኩባንያውን ልዩ የሚያደርገው በገበያ ዋጋ ላይ ያልተመሠረተ ሥራ መሥራቱ ሲሆን፤ የምርቶች የገበያ ዋጋ ምንም ይሁን ምን ፐርፐዝብላክ ምርቶችን ከእርሻ ወይም ከፋብሪካ ባመጣበት ዋጋ ላይ 10 በመቶ የአገልግሎት ክፍያ ብቻ በማስከፈል ምርቶችን ለገበያ የሚያቀርብ መሆኑ ነው። ይህንን ዓላማውን በተሳካ ሁኔታ ለማስፈጸም ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አራት ስልቶችን ነድፎ እየተገበረ የሚገኝ ሲሆን በእነዚህ የማስፈጸሚያ ስልቶች አማካይነት የተገኙ ውጤቶችን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

- **የከገበሬው ሱፐርማርኬቶች፡** በምርት ስርጭት እና ግብይት ዘርፍ ያሉ ሥራዎችን ስኬታማ በሆነ መልኩ ለማስኬድ ከተነደፉ ስልቶች አንዱ ኩባንያው የራሱ የሆነ የችርቻሮ መደብሮችን መክፈት ሲሆን ስያሜያቸውም **ከገበሬው ሱፐርማርኬት** የሚባሉ ናቸው። በዚህ ስልት አማካይነት ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በአምስት ዓመታት ውስጥ በመላ አገሪቱ 1,000 ከገበሬው ሱፐርማርኬቶችን ለመክፈት ግብ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን እስከ አሁን በአዲስ አበባ ስምንት ሱፐርማርኬቶችን ለመክፈት ችለናል። እነዚህም በአያት ፣ በሰሚት ፣ በዓድዋ ድልድይ/አባሬ/ ፣ በሳርቤት ፣ በቡልቡላ ፣ በላፍቶ፣ በሜክሲኮ ፣ እና በጎፋ አካባቢዎች የሚገኙ ናቸው። ወቅቱም ልምድ የምንቀስምበትና ትምህርት የምንወስድበት በመሆኑ በፍጥነት ማስፋፋትን በተመለከተ መረጃን መሠረት ባደረገ መልኩ ለማስኬድ ጥናቶችን በማካሄድ ላይ እንገኛለን። አሁን ባለበት ሁኔታ የሱፐርማርኬቶቹ የዕለት ሽያጭ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የደረሰ ሲሆን ፤ በሒደትም ሽያጫቸውን በብዙ እጥፍ የሚያሳድጉበትን የተለያዩ የሽያጭ ስልቶች በመንደፍ በመተግበር ላይ እንገኛለን። ለአብነት ያህልም በሽንኩርት እና በዳቦ ላይ የጀመርናቸው አብዮቶችን መጥቀስ የሚቻል ሲሆን ሽንኩርትን በኪሎ በ25 ብር እንዲሁም 100 ግራም ዳቦ /ዋና የሆነውን የዱቄት ግብአት ከሰንዴ ፣ ማሽላ ፣ ገብስና ፣ በቆሎ በመቀላቀል/ በብር 4.50 መሸጥ ከጀመርን ሰነባብተናል። በእነዚህ እንቅስቃሴዎቻችን የተነሣ ለሰፊው ሕብረተሰብ እና አግባብነት ላላቸው

ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ቃላችንን በተግባር የምንፈጽም ስለመሆናችን ማንነታችንን ለማሳየት የቻልን ሲሆን ፤ ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡልን በትብብር እንሥራ የሚሉ ጥያቄዎች ከዕለት ዕለት በከፍተኛ ቁጥር በመጨመር ላይ ይገኛሉ። ዓላማችንም "**ከገበሬው**" የሚለውን ስያሜ በሁሉም ቤተሰቦች ዘንድ የሚታወቅ እና ሠርክ የሚጠራ ስያሚ(ብራንድ) እንዲሆን ማድረግ ሲሆን ይህንንም እያሳካን ለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሰጡ መረጃዎችን ለማጠናቀር ተችሏል።

- **እሰቤዛ ለሁሉም፥** ሌላውና ዋነኛ የዚህ ዘርፍ የማስፈጸሚያ ስልት ተደርጎ የተወሰደው እሰቤዛ ለሁሉም ማቅረብ የሚለው ስልታችን ነው። በዚህ ስልት አማካይነት በመንግሥት፣ በግል እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች መስሪያ ቤቶች ለሚሠሩ ሠራተኞች እንዲሁም በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ከመሥሪያ ቤቶቹ ወይም ከነዋሪዎች ማኅበር በኩል በሚቀርብልን ጥያቄ መሠረት እሰቤዛን በዱቤ መሥሪያ ቤታቸው ደረስ አሊያም የጋራ መኖሪያ ቤታቸው ደረስ እናቀርባለን። የሠራተኞቹ ወይም የጋራ መኖሪያ ቤቶቹ ነዋሪዎች ብዛት ከ150 ካለፈ እዚያው በተቋማቱ ወይም በጋራ መኖሪያ ቤቱ አካባቢ የራሳችንን የእሰቤዛ ሱቆች በመክፈት የዕለት ፍጆታ ምርቶችን በማቅረብ ላይ እንገኛለን። በዚህ ስልት አማካይነት እስከአሁን ባለው ሒደት ከመቶ ለሚያልፉ ተቋማት እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ምርት እያቀረብን ሲሆን ሒደቱም እጅግ የሚያበረታታ እና ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ አግኝተነዋል። ጥያቄዎች ከመዲናችን አዲስ አበባ አልፈው ከክልል ከተሞችም እየመጡልን ሲሆን እኛም የውስጥ አቅማችንን በማሳደግ መደረሻዎቻችንን ለማስፋት ከፍተኛ ርብርብ እያደረግን እንገኛለን። የዱቤ አገልግሎት ሥርዓቱንም የበለጠ ለማሳለጥና የተዋጣለት አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለን ከተለያዩ የዱቤ አገልግሎት አቅራቢ ባንኮችና መሰል የፋይናንስ ተቋማት ጋር በጋራ እየሠራን እንገኛለን። በተቋማቱ በኩል እየተሰጠን ያለው ምላሽም እጅግ ተስፋ ሰጪ ነው።

- **ለትላልቅ ተቋማት የጅምላ ምርት አቅርቦት /Corporate Sales/፥** በዚህ ሦስተኛ ስልት አማካይነት ኩባንያአችን እንደ ሆቴል፣ ሆስፒታል፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ግብረ-ሠናይ ድረጅቶች፣ የወታደር ካምፖችና… ለመሳሰሉት ለተጠቃሚዎቻቸው የዘወትር ምገባ አገልግሎት ለሚሰጡ ትላልቅ ተቋማት ምርትን በጅምላ እና በዱቤ አገልግሎት የሚያቀርብ ሲሆን ይህም ኢትዮጵያን እንመግብ በሚለው ታላቅ አገራዊ አጀንዳችን ማዕቀፍ ውስጥ ለሁሉም ተደራሽ የመሆን ዕቅዳችን አንዱ አካል ነው። እስከአሁን ባለው ሒደትም 112 ለሚደርሱ ትላልቅ ተቋማት ምርትን በጅምላ እና በዱቤ አገልግሎት እየቀረብን ሲሆን ይህንንም ሥራ እጅግ በማሳደግ ታላቅ አገራዊ ተጽዕኖ ፈጣሪ ኩባንያ ሆነን ለመውጣት ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን እንገኛለን።

- **ከገበሬው ኢኮሜርስ /Kegeberew Ecommerce; kegeberew.com/፥** በዚህ አራተኛ የግብይት ማሳለጫ ስልታችን አማካይነት ሸማቾች ምርትን ካሉበት ሆነው ከገበሬው ደት ኮም በሚል የበይነ-መረብ አማራጭ ወይም በ9858 ነጻ የስልክ ጥሪ ማእከል በመጠቀም ትዕዛዝ በማቅረብ ግብይት የሚፈጽሙበት ጊዜው በደረሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃ በመጠቀም የሚተገበር ስልት ሲሆን ፤ በዚህ ስልት አማካይነትም ኩባንያችን በኢትዮጵያ ግዙፉ የበይነ-መረብ መገበያያ መደረክ ሆኖ መውጣትን እንደ አምስት ዓመት ዕቅዱ ነድፎ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በመተግበር ላይ ይገኛል። **ሁሉም ነጋዴ ፤ ሁሉም አካፋፋይ ፤ ሁሉም ሠራተኛ** የሚለውም የዚህ የበይነ-መረብ ግብይት መድረክ መርሕ ሲሆን ፤ ይህ የበይነ-መረብ ግብይት መድረክ ከዕለት ፍጆታ ምርቶች በዘለለ ማንኛውንም ለቤትና ለመሥሪያ ቤት ተፈላጊ የሆኑ እንደ ፈርኒቸር ፣ ኤሌክትሮኒክስ ፣ መድኃኒቶች ፣ የሕፃናትና የአዋቂ ልብሶች ፣ የስፖርት ትጥቆች… የመሳሰሉትንም ለመገበያየት የሚያስችል /Multi-vendor/ የበይነ-መረብ ግብይት ማእከል ነው። በዚህ የበይነ-መረብ ግብይት ዘርፍ በመላ አገሪቱ በሁሉም ወሳኝ ቦታዎች ምርትን ማሰባሰቢያ፣ ማከማቻ እና ማዘጋጃ /ማለትም Product Sourcing, Storage & Fulfilment/ ማእከላትን በመክፈት ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ይበልጥ ተደራሽ የሆነ አገልግሎት /Nationwide Distribution Service/ ለመስጠት ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህ የበይነ-መረብ ግብይት መድረክ እስከ አሁን በቀን ከ1,000–2,000 የሚደርሱ ትዕዛዞችን ተቀብለን እያስተናገድን ሲሆን ውስጣዊ አቅማችንን ከዕለት ዕለት በማሳደግ በየቀኑ በአሥር እና መቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ደንበኞችን ተቀብለን ለማገልገል የዝግጅት ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ እነዚህን እጅግ ግዙፍ የሆኑ፣ ወጥነት ያላቸው እና የተቀናጁ የግብርና እሴት ሰንሰለቱ ላይ የተመሠረቱ ሥራዎች በተዋጣለት መልኩ ለማካሄድ ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ ማፍሰስ እንደሚኖርበት ቀደም ብሎ ተገንዝቧል። በመሆኑም ሰፋፊ እና በዓይነታቸው ልዩ የሆኑ የካፒታል ሞቢላይዜሽን ስልቶችን በመጠቀም ሲሠራ ቆይቷል። በእነዚህ በዓይነታቸው ልዩ የሆኑ የካፒታል ሞቢላይዜሽን ስልቶች አማካይነትም ኩባንያው በተመሠረተ በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ካፒታሉን ከ1.1 ሚሊዮን ብር ወደ 2.4 ቢሊዮን ብር ማሳደግ የቻለ ፤በዘርፉ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት ዕድገትን ያስመዘገበ፤ በሥራው የሚያኮራ ፤እና የአክሲዮን ባለቤቶቹን የካፒታል ኢንቨስትመንት መጠን በብዙ እጥፍ እንዲያድግ ያደረገ ኩባንያ ለመሆን ችሏል።

በዚህም አግባብ ዋጋቸው 100 ብር የሆኑ እና ዝቅተኛ የአክሲዮን መግዛ መጠናቸው 10 የሆነ ባለ 1,000 ብር መደበኛ አክሲዮኖችን በመሸጥ የጀመረው ኩባንያችን በሒደት ልዩ ጥቅም የሚያስገኙ ከ100,000 ብር የሚጀምሩ የፍራንቻይዝ አክሲዮኖችን ያስተዋወቀ ሲሆን በዚህ ሳያበቃ 1.5 ሚሊዮን ብር በአንድ ጊዜ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለአክሲዮኖች አሁንም ልዩ የቤት ባለቤትነት ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን TSM የተባለ የTower Shareholder Model በማስተዋወቅ በሒደቱም ከፍተኛ ገንዘብ ማሰባሰብ ተችሏል። ይህም በዚህ በያዝነው የሪፖርት ዓመት የተፈጸመ ተግባር በመሆኑ እጅግ ልንኮራ ይገባል ባይ ነን። በዚህም አግባብ እስከ አሁን ባለው ሒደት፦

- መደበኛ ባለአክሲዮኖች ቁጥር 6,222
- የተቀናጀ ግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ፕሮግራም ስር የታቀፉ ገበሬ ባለአክሲዮኖች ቁጥር 10,503
- የፍራንቻይዝ ባለአክሲዮኖች ቁጥር 2,199
- TSM ባለአክሲዮኖች ቁጥር 1,284 የደረሰ ሲሆን
- በድምሩ ኩባንያው 20,218 ባለአክሲዮኖች እንዲኖሩት አስችሎታል።

በዚህና ሒደቱ በወለዳቸው ሌሎች የካፒታል ማሰባሰቢያ ስልቶች አማካይነት የድርጅቱን ካፒታል ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ2.4 ቢሊዮን ብር በላይ እንዲሆን ለማድረግ ተችሏል። ይህም እጅግ የሚያኮራ ተግባር ነው።

በልዩ ሁኔታ ከተዘጋጁት አክሲዮኖች መካከል የፍራንቻይዝ አክሲዮን ሞዴል 100,000 ብር እና ከዚያ በላይ ኢንቨስት ላደረጉ ባለአክሲዮኖች እንደፍላጎታቸው ከአንድ ሄክታር መሬት ልማት ላይ ከሚገኝ ቀጥተኛ ትርፍ ወይም ከአንድ የግብርና ምርቶች ማቀናበበሪያ የኒት ላይ ከሚገኝ ቀጥተኛ ትርፍ ላይ 50 በመቶ የትርፍ ተካፋይ እና በገዙት አክሲዮን መጠን ደግሞ ጠቅላላ ጉባኤው በሚወስነው መሠረት ዓመታዊ የትርፍ ክፍፍል ተካፋይ የሚሆኑበት ዕድል የሚፈጥርላቸው ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

በተመሳሳይም TSM የተባለው የ Tower Shareholder Model በአንድ ጊዜ 1.5 ሚሊየን ብር ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለአክሲዮኖች በገዙት የአክሲዮን መጠን ልክ የዓመታዊ ትርፍ ክፍፍል ተካፋይ ከመሆናቸው ባሻገር በልዩ ሁኔታ ኩባንያው ወደፊት በሚያስገነባው የከገበሬው ታወር ኮምፕሌክስ ውስጥ 100 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ባለ ሦስት መኝታ ክፍል የአፓርትመንት ቤት ባለቤት ለመሆን የሚያስችል ልዩ ዕድል ነው።

በዚህ አጋጣሚ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በአገራችንም ሆነ በአፍሪካ እጅግ ግዙፍ የሆነውን ባለ 115 ወለል የከገበሬው ታወር የሚል ስያሜ ያለው ሕንጻ ለመገንባት ባዘጋጀው ውጥን አማካይነት በአሁኑ ሰዓት ሜክሲኮ የሚገኘውን የቢጂአይ ዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ እና በዙሪያው ያለውን ለመልማት ዝግጁ የሆነ 30,000 ካሬ ሜትር የሚደርስ መሬት በመግዛት ይህንን በዓይነቱ ልዩ የሆነ ዓለም አቀፍ የገበሬው ምስጋና ታወር ለማስገንባት በከፍተኛ ርብርብ ላይ ይገኛል። በዚህም ታዳሚውን እንኳን ደስ አለን ማለት እንፈልጋለን። ይህ የመገንቢያ ቦታ ሙሉ በሙሉ በእጃችን ገብቶ እንቅስቃሴ በምንጀምር ወቅት በኢትዮጵያ ትልቁን ታሪክ የምንሠራበት የጅማሮ ሒደት ሆኖ በታሪክ የሚመዘገብ ይሆናል።

በዚህ TSM በተባለው ሞዴል አማካይነት ኩባንያችን ለሕዝብ ክፍት አድርጓቸው የቆየው ውስን የአክሲዮንና የቤት ባለቤትነት ዕድሎች ተጠቃሚ ለመሆን ከመጡት ገዢዎች ለመረዳት እንደተቻለው በአገራችን በተለይም ደግሞ በመዲናችን አዲስ አበባ ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት እጥረት ያለ መሆኑንና ሰዎች ባለቸቸው ውስን ጥሪት ሃብት የራሳቸውን ቤት ለመግዛት ቢፈልጉ እንኳን የመኖሪያ ቤት ዋጋ ለአብዛኛው ነዋሪ የማይቀመስ መሆኑን ለማስተዋል ተችሏል።

Purpose Black

በመሆኑም የኑሮ ውድነትን ከመዋጋት ጋር በተያያዘ ከዕለት ፍጆታ የምግብ ምርቶች በተጨማሪ መጠለያም አንዱ ተዋናይ እንደሆነ ስለታመነበት ፤ በጥናቶችም እንደተረጋገጠው የኑሮ ውድነትን ከሚያመጡ ነገሮች ውስጥ 54 በመቶው ምግብ እና 16 በመቶው ደግሞ መጠለያ በመሆኑ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በዚህ በያዝነው የሪፖርት ዓመት **ቤት ለሁሉም /Home for Everyone/** በሚል መርሕ የከገበሬው ሪል እስቴት የተባለ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሙን ይፋ አድርጓል። በዚህ የከገበሬው ሪል እስቴት ኢንተርፕራይዝ ውስጥ እንዲተገበሩ ከተነደፉት አራት ዋና ዋና ተግባራት አንዱ ቤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሁሉም የከተማ ነዋሪ ለማቅረብ የተነደፈው Affordable Housing Program ነው። በዚህ ፕሮግራም አማካይነት ከአምስት እስከ አሥራ አምስት ወለል ያላቸው መኖሪያ ቤቶችን እጅግ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ሰርቶ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ ዝግጅቶች የተጠናቀቁ ሲሆን የቤት ባለቤትነት ምዝገባም ለመጀመር ዝግጅቶች እየተጠናቀቁ ይገኛል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሁሉንም ነገር በተቻለ መጠን በራስ አቅም መሥራት በሒደትም የከገበሬው ኢኮኖሚያዊ ስነ ምሕዳርን /Kegeberew Economic Ecosystem/ መገንባት በሚለው መርሑ አማካይነት የተለያዩ አዳዲስ ፕሮጀክትና ፕሮግራሞችን እየነደፈ "**ከገበሬው**" በሚለው የብራንድ ስሙ አማካይነት እያስተዋወቀ እና እየተገበረ የሚገኝ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል።

- ቤት ለሁሉም በሚል መርሕ ቤቶችን እጅግ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለሰፊው ማኅበረሰብ ማድረስን እንደ አንድ ዋነኛ ግቡ ነድፎ ለመንቀሳቀስ የዝግጅት ሥራውን ያጠናቀቀው ከገበሬው ሪል እስቴት ኢንተርፕራይዝ /Kegeberew Real Estate Enterprise/

- በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሚሆነው የንግድ ወይም የመገበያያ ቴሌቪዥን ከገበሬው ቲቪ /Kegeberew TV/

- ሁሉንም ዓይነት ጊዜው የደረሰባቸውን የቴክኖሎጂ ግብአቶችን በመጠቀም አዳዲስ እና ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓቶች እንዲኖሩ የሚያደርግና ከፐርፐዝብላክ አልፎ ለሌሎችም የቴክኖሎጂ ሶሉሽን አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ውጥን የተያዘለት ከገበሬው ቴክኖሎጂ ሶሉሽንስ ኢንተርፕራይዝ /Kegeberew Technology Solutions Enterprise/

- **አፍሪ ቡና/Afri-Buna/** በሚል ልዩ የብራንድ ስያሜ በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆንና የኢትዮጵያንና የአፍሪካን የቡና ባህል በከፍተኛ ሁኔታ በዓለም ያስተዋውቃል ተብሎ የታመነበት ከገበሬው ቡና ኢንተርፕራይዝ /Kegeberew Coffee Enterprise/

- ከእንጨት፣ ከብረት እና ፍልፍል ድንጋይ የሚሠሩ ሁሉንም ዓይነት የቤትና የቢሮ የእደጥበብ ሥራ ውጤቶችን በሰፊው በማምረት ለሁሉም የፐርፐዝብላክ የሥራ ክፍሎች አገልግሎቶችን ከመስጠት በዘለለ ሌሎች አገልግሎቶችንም በማቅረብ ትልቅ የገቢ ምንጭ ማስገኛ ዘርፍ እንዲሆን ውጥን የተያዘለት ከገበሬው ክራፍትስ ኢንተርፕራይዝ /Kegeberew Crafts Enterprise/

- ተፈላጊ የሆኑ የማስታወቂያ ሥራዎችን በተለያዩ የሕትመት ሚዲያዎች በመጠቀም ለፐርፐዝብላክ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር ለሌሎችም ተደራሽ እንዲሆን ውጥን የተያዘለት ከገበሬው ሕትመትና ፓኬጂንግ ኢንተርፕራይዝ /Kegeberew Printing and Packaging Enterprise/ ይገኙበታል።

በተጨማሪም በጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም. የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የዳይሬክተሮች ቦርድ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከዚህ በኋላ የ Holding Company Status ኖሮት እንዲቀጥል በውስጡ ያሉ ዋና ዋና የሥራ ክፍሎችም ራሳቸውን የቻሉ የፐርፐዝብላክ እህት ኩባንያዎች ሆነው እንዲወጡ በወሰነው መሠረት አሥራ ስድስት (16) የሚደርሱ የሥራ ክፍሎች በመጀመሪያው ዙር ወደ ራሳቸውን የቻሉ እህት ኩባንያነት እንዲሸጋገሩ አቅጣጫ አስቀምጦ በማስተግበር ላይ ይገኛል። እነዚህም፦

- በግብርና ልማት እና በግብርና ምርቶች ማቀነባበር ላይ የሚያተኩር የከገበሬው አግሪብቢዝነስ ኢንተርፕራይ (Kegeberew Agricultural Businesses Enterprises)

- በምርት ማሰባሰብ እና ስርጭት ላይ የሚያተኩር የከገበሬው ሎጂስቲክስ እና የምርት ስርጭት ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Logistics, Product Sourcing and Distribution Enterprise)

- በመኖሪያ ቤቶች ፣ የንግድ ማእከላት እና የቢሮ ግንባታ ሥራዎች ፣ እንዲሁም በንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የሚያተኩር የከገበሬው ሪል እስቴት (Kegeberew Real Estate)
- በወጪና ገቢ ንግድ ላይ የሚያተኩር የከገበሬው ኤክስፖርት ኢምፖርት ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Export and Import Enterprise):
- ሁለገብ የፋይናንስ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ተደርጎ የሚዋቀር የከገበሬው የፋይናንስ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Financial Services Enterprise)
- የከገበሬው የፖሊሲ ጥናትና የቢዝነስ ዴቨሎፕመንት አገልግሎት አቅራቢ ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Policy Studies and Business Development Enterprise)
- የከገበሬው ማርኬቲንግ እና ሴልስ ሶሉሽንስ ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Marketing and Sales Solutions Enterprise)
- የከገበሬው ቴሌቪዥን (Kegeberew Television)
- በቴክኖሎጂ አገልግሎት ሥራዎች ላይ በሰፊው የሚሠራ የከገበሬው ቴክኖሎጂ ሶሉሽንስ ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Technology Solutions Enterpirse)
- የቡናን ንግድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያከናውነው ከገበሬው ቡና ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Coffee Enterprise)
- የከገበሬው ክራፍትስ ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Crafts Enterprise)
- ከገበሬው ሕትመትና ፓኬጂንግ ኢንተርፕራይዝ (Kegeberew Printing and Packaging Enterprise)
- የከገበሬው ኬተሪንግ ሰርቪስ (Kegeberew Catering Services)
- የከገበሬው አጠቃላይ ሕንጻ ተቋራጭ Kegeberew General Construction
- ከገበሬው ሰሚንቶ ፋብሪካ (Kegeberew Cement Factory)
- ከገበሬው የብረታ ብረት ፋብሪካ (Kegebere Steel Structure Production and Distrbution Enterprise) ናቸው።

እንግዲህ የፐርፐዝብላክ የሁለት ዓመት ተኩል የእድገት ጉዞ እና የአንድ ዓመት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርትን ከዚህ በላይ ባስቃኘናችሁ መሠረት የቀረበ ሲሆን መንገዱ ግን ማንም እንደሚያስበው አልጋ በአልጋ ሳይሆን እጅግ ውስብስብ በሆኑ ተግዳሮቶች የታጀበ ነበር። የሥራው ተፈጥሮም የግብርናው የእሴት ሰንሰለት ላይ ያተኮረ መሆኑ ተግዳሮቶቹ የበለጠ ከባድ እንዲሆኑ ምክንያት ሆኗል። ዋና ዋና ከሚባሉ ተግዳሮቶች ውስጥ የሚከተሉትን ለአብነት አቅርበናል።

- በአገሪቱ በየአካባቢው የሚስተዋሉ ግጭቶች እና የሰላም እጦቶች በአጠቃላይ የድርጅቱ የሥራ ሒደት ላይ ከፍተኛ የደኅንነት ስጋት የጣሉ እና ሥራዎች በተፈለገው ፍጥነት እንዳይሄዱ ያደረጉ ሲሆን በተለይ ደግሞ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች በምናደርጋቸው የእርሻ ልማት ሥራዎቻችን ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ፈጥረውብናል። በዚህ የደኅንነት ችግር የተነሣ በአማራ ክልል በተለያዩ ቦታዎች ያደራጀናቸውን የገበሬ ክላስተሮች ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ባለመቻላችን ጅምር ጥረቶቻችን መክነዋል። የደኅንነት ችግሩ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በማሰባሰብ ሒደቱ ላይ ከፍተኛ ደንቃራ የፈጠረብን ሲሆን በተደጋጋሚ በሚከሰት የጉዞ መስተጓጎል የተነሣ ምርትን እንደልብ ማቅረብ ባለመቻላችን በከፍተኛ ጥረት ያስነበትናቸውን ነባር ደንበኞቻችንን እስከማጣት እና በመሠረታዊ ምርቶች ላይ ያልተገባ ጭማሪ እንዲኖር መንስኤ ሆኗል። ምርቶች በመንገድ ላይ ያለምንም በቂ ምክንያት ታግደው ተወርሰውብናል። ሹፌር ተገድሎብናል። ባለሙያዎቻችን ተደብድበውብናል። መኪኖች ተገደው ለግዳጅ ሥራ ተወስደውብናል።

- በምንሠራቸው ሥራዎች እና በምንተገብራቸው ስልቶች በመደንገጥ የተዛባ መረጃ ለሕዝቡ እንዲደርስ ሲያደርጉ የነበሩ ጥቂት የሪል እስቴት ባለቤቶች እና በጥቅም የተገዙ የማኅበራዊ ሚዲያ አቀንቃኞች በድርጅታችን መልካም ስም እና ተግባር ላይ ያልተገባ ጥላሸት በመቀባት ጊዜያዊም ቢሆን እጅግ ፈታኝና ከባድ ተግዳሮት ያሳረፉብን ሲሆን የፋይናንስ እንቅስቃሴያችንን እስከማሳገድ ደርሶ በድርጅቱ አጠቃላይ ህልውና ላይ ፈታኝ ክንዱን አሳርፎ ለማስፍ ችሏል። በሒደቱም እጅግ ለማደግና ለመመንጠቅ የሚያስችሉ ወርቃማ ዕድሎቻችንን ለመጠቀም ሳንችል እንድንቀር ሆኗል። የ ባይሆን ኖሮ ዛሬ ላይ ቆመን የምንነግራችሁ ታሪክ ከዚህ በብዙ እጥፍ የተሻለ እና በሐሴት የተሞላ ይሆን ነበር። በዚህ አጋጣሚ የተከሰተው ችግር እንዲፈታ የድርጅታችን ባለ ድርሻዎች ከቦርዱና ማኔጅመንቱ ጋር በፍጹም የዓላማ ጽናት በመቆም ኮሚቴም በማቋቋም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግሥት አስፈጻሚዎች በአካል በማነጋገርና በማሳመን ችግሩ ባስቸኳይ እንዲፈታ ላደረጋችሁት እጅግ ከፍተኛ ድጋፍ ቦርዱና ማኔጅመንቱ የላቸውን ከበሬታና ከልብ የመነጨ ምስጋና ለማቅረብ እንወዳለን።

- በተወሰኑ ቦታዎች የሚታየው የተንዛዛ ቢሮክራሲ እና ብልሹ አሠራርም የልማት እንቅስቃሴዎቻችንን በምንፈልገው ፍጥነት ማስኬድ እንዳንችል አድርጎናል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ለመጥቀስ ያህል ከተለያዩ የክልል መንግሥታት የጠየቅናቸው የግብርና ኢንቨስትመንት መሬቶች ከባለስልጣኖች ሙሉ ፈቃደኝነት ያለ ቢሆንም በየደረጃው ባሉ አስፈጻሚዎች ለመፍቀድ ጊዜ የወሰደባቸው በመሆኑ መሬት የወረዱ ሥራዎቻችን ከትልሞቻችን ጋር ብዙ የተራራቁ እንዲሆኑ አድርገውብናል፡፡ ከመሠረታዊ የምግብ የፍጆታ ምርቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይነሣ ብለን የጠየቅነው ጥያቄ አግባብነቱ ታምኖበት የባለስልጣናትን ይሁንታ ያገኘ ቢሆንም እስከ አሁን በአዋጅ ጸድቆ ተግባራዊ መሆን አልቻለም፡፡ ይህ ሁሉ የተንዛዛ ቢሮክራሲና አልፎ አልፎም የብልሹ አሠራር ውጤት ነው፡፡ በሥራችን ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተጽዕኖም ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

- የኢንተርኔት እና ተዛማጅ የስልክ አገልግሎት መቋረጥ እና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ማግኘት አለመቻል አንዱ ትልቁ ተግዳሮታችን ነበር፡፡ በነጻ የጥሪ ማእከሎቻችን የምናስተናግደውን የደንበኛ መጠን በብዙ እጥፍ ለማሳደግ ከፍተኛ ርብርብ እያደረግን ቢሆንም ከቴሌኮም አገልግሎት አቅርቦት አንጻር የሚታየው ዳተኝነትና የትብብር ማነስ የከፋ ነው፡፡

- በአገሪቱ በፍጹም ለማሰብ በሚከብድ ደረጃ የብቁ ባለሙያ እጥረት ያለ ሲሆን ታማኝነት /Professional Integrity/፣ በራስ ተነሳሽነት እና በትንሽ ሱፐርቪዥን መሥራት የማይታሰቡ እስኪመስሉ ድረስ ችግሮችን አስተውለናል፡፡ በመሆኑም እነዚህ በባለሙያዎች ዘሪያ ያስተዋልናቸው የአቅም ፣ የተነሳሽነት እና የእምነት ችግሮች ትላልቅ የሆኑ ሥራዎቻችን ላይ ያሳረፉት አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላል የሚታይ አልነበረም፡፡

- በመጨረሻም በአገሪቱ የተከሰተው እና ለዓመታት መፍትሄ ያልተገኘለት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ከላይ ከተገለጹት ችግሮች ጋር ተደምሮ የኢንቨስትመንት ሥራዎቻችን ላይ እጅግ ከፍተኛ ተግዳሮቶችን የፈጠረብን ሲሆን በተለይም የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ግብአቶችን ፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እና ማሽነሪዎችን ከውጭ ለማስመጣትና ወደ ሥራ ለማስገባት ባለመቻላችን ሥራዎቻችንን በምንፈልገው ፍጥነትና ጥራት ማካሄድ ሳንችል ቀርተናል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ሁላችሁም እንደምታውቁት ለማንኛውም ድርጅት በተለይም እንደኛ ግብርና ላይ ለተሰማራ ድርጅት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሃብት ማሰባሰቢያና የኢንቨስትመንት ዓመታት እንደመሆናቸው መጠን ትኩረቱ ትርፍ ማግኘት ላይ ሳይሆን ትርፍ ሊያመጡ የሚችሉ ኢንቨስትመንቶች ላይ መሥራት ነው። ደግመን ደጋግመን ድርጅቱን ስንመሠርት ግልጽ እንዳደረግነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ትርፍ ማግኘት የሚፈልግ ኢንቨስተር ፐርፐዝብላክ ላይ ሳይሆን ሌሎች መስኮች ላይ ኢንቨስት እንዳያደርግ ስንመክር ቆይተናል።

ያለፈው ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴያችንም የሚያንጸባርቀው ይህንኑ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሲሆን በዚህም ምክንያት በዓመቱ የሒሳብ ሪፖርታችን ከትርፍ ይልቅ የኪሳራ ልዩነት ቢያሳይም ተቋማችን በተለያዩ የተቋም የሒሳብ መመዘኛዎች ግን በእጅግ ጥሩ ቁመና ላይ እንዳለ ያሳያል። ተቋማችን በአሁኑ ሰዓት አዎንታዊ የሆነ የcash flow እና ከፍተኛ በእጅ ያለ ገንዘብ (liquid cash) ያለው ሲሆን ፤ ሌሎቹን የሒሳብ መመዘኛዎች በተመለከተ ካለፈው ዓመት የሒሳብ አቋማችን ጋር ሲነጻጸር ይህንን ይመስላል።

Purpose Black ETHIOPIA

## Comparative Balance Sheet for the Year End 2015 vs 2016, (Interim)

| Category | 2016ec (interim) ' ETB Millions" | 2015ec ' ETB Millions" | Change in value ' ETB Millions" | Change in Percentage Δ% |
|---|---|---|---|---|
| **Equity & Liability** | | | | |
| **Shareholders Fund** | | | | |
| Registered Capital | 1.1 | 1.1 | .0 | 0% |
| Share | 2033.6 | 1775.8 | 257.9 | 15% |
| **Non-Current Liability** | | | | |
| Long term borrowing | 29.5 | 10.0 | 19.5 | 195% |
| **Current Liabilities** | | | | |
| Trade Payable | | | | |
| Advance Real Estate Sales | 844.1 | 15.9 | 828.2 | 5208% |
| Taxes Payable | 18.8 | 12.5 | 6.3 | 50% |
| Other payable | 1.5 | 2.6 | -1.1 | -42% |
| **Total** | **2407.2** | **1531.2** | **876.0** | |
| **Assets** | | | | |
| **Non-Current Assets** | | | | |
| Fixed Assets | 241.7 | 39.8 | 201.9 | 507% |
| Property purchase on progress | 1056.9 | 921.3 | 135.6 | 15% |
| Investment | 83.5 | 6.5 | 77.0 | 1183% |
| **Current Asset** | | | | |
| Trade Receivables | 98.0 | 83.5 | 14.5 | 17% |
| Inventory | 50.6 | 42.1 | 8.6 | 20% |
| Cash & Bank | 794.9 | 294.7 | 500.2 | 170% |
| VAT Receivable | 34.1 | 139.8 | -105.6 | -76% |
| Withholding Receivable | .2 | .2 | .0 | 27% |
| Advance & Prepayments | 47.1 | 3.3 | 43.8 | 1312% |
| **Total** | **2407.2** | **1531.2** | **876.0** | |

እንግዲህ በዚህ ባሳለፍነው አንድ ዓመት ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የነደፋቸውን ትላልቅ ትልሞች ለማሳካት ደፋ-ቀና እያለ የነበረ ሲሆን ባሳለፍነው ዓመት የ 221,690,786.00 ብር የሒሳብ ኪሳራ በእኛ አጠራር የኢንቨስትመንት ልዩነት ቢያሳይም በማናቸውም መስፈርቶች ሲታይ ግን ባለፈው አንድ ዓመት የተመዘገቡት ውጤቶችና የተቋሙ የእድገት ደረጃ በተጨባጭ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ የድርጅቶች ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ታሪክ የተሠራበት ዓመት የነበረ ሲሆን ይህም ተቋሙን በጥሩ የፋይናንስና ድርጅታዊ መሠረት ላይ በማስቀመጡ ባለፈው ጠቅላላ ጉባኤ በገባነው ቃል መሠረት በሚቀጥለው ዓመት ለተቋሙ ባለ አክሲዮኖች ትርፍ ለመስጠት እንቅስቃሴያችንን የጀመርን መሆኑን ስናሳውቅ በደስታ ነው። ይህም በመሆኑ የዘንድሮውን የጠቅላላ ጉባኤ መሪ ቃል "Turn-around General Assembly" ወይም ከኢንቨስትመንት ወደ ትርፍ ብለን የሰየምነው ሲሆን እንዴት ይህንን ትርፍ ለማምጣት እንዳሰብን እጅግ ግልጽ የሆነ "The Road-Map to 25% ROI" ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀት ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንኛለን። ይህም ፍኖተ ካርታ በዛሬው ዕለት ከዚህ ሪፖርት በኋላ በዋና ሥራ አስፈጻሚያችን አማካኝነት ለጠቅላላ ጉባኤው የሚቀርብ ይሆናል።

ተቋማችንም ከላይ የተመዘቡትን ውጤቶች ማስመዘገብ የቻለው እጅግ ፈታኝ ወቅቶችንና አንኳር ተግዳሮቶችን በማለፍ ነው። ለምሳሌ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል ባጋጠመው የፀጥታ ችግር(ጦርነት) ምክንያት ኢንቨስትመንት መቋረጥ፣ ምርትን ከቦታ ወደ ሌላ ቦታ ወይም ክልል ለመውሰድ አለመቻል ፤ ሀብት ላይ የሚደርሱ አደጋዎች እንዲሁም ስርቆት ፤ የኀይል መቆራረጥ ፤ ማጭበርበር ፤ ብልሹ አሠራር፣ በታችኛው የመንግሥት መዋቅር የግንዛቤ አለመኖር ፤ ከልክ በላይ ቢሮክራሲ ማብዛት ፤ የግብአቶች እጥረት ፤ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ፤ አንዳንድ ግብዓት በአገር ውስጥ ያለመገኘት፣ የገበያ አለመረጋጋትና የኀይል አቅርቦት መቆራረጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ተግዳሮቶች ነበሩ።

የተገኙትም የተግባር ውጤቶች በዘጠኙ ቦርድ አባላትና በዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍሥሐ እሸቱ በብዙ ትዕግስት ፤ በብልሃትና በአስተዋይነት በመምራት እና የፈጣሪ እገዛ ታክሎበት ጭምር ነውና በቅድሚያ ፈጣሪያችንን ማመስገን ፤ በመቀጠልም በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ ያለምንም መሰልቸት ራዕዩን እና ተልዕኮውን ብቻ የትኩረታቸው አቅጣጫ አድርገው በቆራጥነት ሲንቀሳቀሱ የነበሩ መላው የፐርፐዝብላክ ቤተሰብ ማለትም የተቋሙ ባለአክሲዮኖች ፤ የቦርድ አመራር አባላት ፣ የማኔጅመንት አባላት ፣ በየደረጃው ያሉ የሥራ ኀላፊዎች እና ተባባሪ አካላት ፣ እንዲሁም መላው ሠራተኛን ከልብ በማመስገን የአንድ ዓመት የሥራ ሪፖርታችንን በዚህ መልኩ እናጠቃልላለን።

ይህንንም ሪፖርት በዚህ መልኩ እንዲቀርብ በተመደቡበት የሥራ ዘርፍ የራሳቸውን ሚና ሲጫወቱ ለነበሩ 1500 ለሚሆኑ የድርጅቱ ሠራተኞች እንኳን ለዚህች ቀን አደረሳችሁ ለማለትና ለማመስገን እንወዳለን።

እናንተም የዚህ ጉባኤ ታዳሚዎች በጉጉት ስትጠብቁት እና የራሳችሁ የሆነውን ኩባንያ ሪፖርት ለማዳመጥ ለነበራችሁ ትዕግስት እጅግ አድርገን እናመሰግናለን። መጪው የልማት ዘመንም ብሩህ እንደሚሆን ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን።

**ከእንቨስትመንት ወደ ትርፍ!!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ሕዝቦቿን ይባርክ።**

**የካቲት ወር 2016 ዓ.ም. አዲስ አበባ።**


ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ
ኑ አብረን እንሥራ!
PURPOSEBLACK ETHIOPIA
COME LET'S WORK TOGETHER
www.purposeblacketh.com